# የቴሌኮሚኒኬሽን መሰረተ ልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን መመሪያ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተመለከተ የፖሊሲ ለውጥ እንዳደረገች ይታወቃል። በዚህም ከዚህ በፊት በመንግስት እጅ ብቻ የነበረው የቴሌኮም ኢንዱስትሪ ለሃገር ውስጥ እና ለውጪ ባለሃብቶች ክፍት እንዲሆን ተደርጓል። ይህን ተከትሎ ከአንድ በላይ የሆኑ የቴሌኮም ኦፐሬተሮች ወደ ስራ ይገባሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በእነዚህ ኦፐሬተሮች መካከል መሰረተ ልማትን እንዲሁም የአገልግሎት ቦታን መጋራት ምን ዓይነት መልክ ሊኖረው እንደሚገባ በአዋጁ ላይ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል[1]።

እነዚህን አጠቃላይ ድንጋጌዎች ወደ መሬት ለማውረድ እና በኦፐሬተሮች መካከል ተገቢ የሆነ የኮሎኬሽን እና የቴሌኮምኒኬሽን መሰረተ ልማት መጋራት እንዲኖር በዘርፉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ማወጣት ያስፈልጋል። ይህን መሰርት በማድረግ የቴሌኮምኒኬሽን መሰረተ ልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በዘርፉ ውጤታማ ስራን መስራት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 44 (5) እና አንቀጽ 44 (10) ላይ መደበኛ የቴክኒክ ደረጃን እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የኮሎኬሽን ቦታን እና የመሠረተልማት መጋራት መመሪያዎችን በተመለከተ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተስጥቷታል። ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54 (2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ሲሆን እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጅ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልከተዋል፤-

- የኔትወርክ አቅምና ብቃት ፣ የማሰራጫና የመቀበያ ጣቢያዎችን፣ ዋና መስመሮችን ፣ ማማዎች እና የኔትወርክ አገልግሎቶች መጋራትን በማበረታታት የኢንቬስትመንት መደራረብ መቀነስ፥
- የኔትወርክ ዝርጋታ ወጪን ዝቅ በማድረግ የአገልግሎት ተጠቃሚው በዝቅተኛ የክፍያ ተመን ጥሩ የሚባል የቴሌኮም አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል እንዲሁም ባሀገሪቱ ውስጥ የኔትወርክ መሠረተ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ፤
- በየቦታው የሚደረጉ የማማ ተከላና ማስፋፋትን በመቀነስ የአካባቢን ውብት እና ደህንነት መጠበቅ፤
- የመሰረተልማት እና የኮሎኬሽን መጋራትን በማበረታታት ዘርፉን ለመቀላቀል ቀላል የሆኑ የመግቢያ በሮችን በመፍጠር በኦፕሬተሮች መካከል የተሻለ ውድድር እንዲኖር ማስቻል፤

## 4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፦** እስካሁን ድረስ የቴሌኮም ዘርፉ ለገበያ ክፍት ባለመሆኑ ከዘርፉ ጋር ተያይዞ የሚነሱ የህግ ጥያቄዎችን በበቂ ሁኔታ የሚያስተዳደር የኢንፍራስትርክቸር እና የኮሎኬሽን መጋራት ትን የተመለከቱ ህግ እና ልምድ አልነበረንም። በመሆኑም ዘርፉን መሰረት ያደረገ ህግ ለመቅረጽ ጥናቶች ማካሄድና በጥልቀት መረዳት የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማሳካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፥ በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ እና የቴክኖሎጂ እድገት በተመለከተ ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነት በረቂቅ መመሪያ ውስጥ ሊካተቱት የሚገባቸው ድንጋጌዎች እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ጉዳዮች ተለይቷል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች መምረጥ፦** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም-አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በመሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለምአቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ ሃገራት ህጎች በሞዴልነት ተመርጠዋል።

- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፡-** ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡-
  - የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለደርሻ አካላትን፣ የሲቪክ ማህበረሰብን፣ ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የህግ ባለሙያዎችን ፣ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር[2] የምክከር መድረክ ተዘጋጅቷል።
  - ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለመሰብሰብ ተችሏል።
  - ባለድርሻ አካላት ያነሱት ነጥቦችን እና ባለስልጣኑ የሰጠውን ምላሽ በተመለከተ ሦስተኛ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል። በዚህ መድረክ ላይ በተሳታፊዎች የተነሱ ነጥቦች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በመመሪያው ላይ ሊካተቱ የሚገቡ ተጨማሪ ግባቶች ተገኝተዋል።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- በመግቢያ (preamble) ክፍል ላይ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች ተለይተው በአንድ ወይም ሁለት ፓራግራፍ ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ፤
- በኮምዩኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካል የመሰረተ-ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄ በሚደረግበት ወቅት የህግ አስፈጻሚ እና የደህንነት ተቋም ላይ ተጽእኖ እንደማይኖራቸው ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
- በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 20(2) ላይ ተጽህኖ ፈጣሪ ኦፕሬተሮች የሚለው ሐረግ ጉልህ ተጽህኖ ያላቸው በሚለው ሐረግ ቢተካ የተሻለ ነው። ይህ በረቂቁ ውስጥ ወጥነት ያለው የቃላት አጠቃቀም እነዲኖር ያስችላል።

[2] https://eca.et/2019/10/10/initial-stakeholder-consultation/

- የዚህን መመሪያ ድንጋጌ በአግባቡ በማይተገብሩ አካላት ላይ ሊወሰድ የሚጣለውን ቅጣት ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ በመመሪያው የልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ክፍል ውስጥ ቢመላከት። በአዋጁ አንቀፅ 52 (4-6) በተመላከተው መሰረት የህግ ማስፈፀሚያ ዝርዝሮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወጥተው ከሆነ በልዩ ልዩ ክፍል ቢካተቱ ያልወጡ ከሆን ደንቡ በቶሎ እንዲወጣ ቢደረግ ይህ ካልሆነ ካለ ደንቡ መመሪያውን ማስፈፀም አዳጋች ያደርገዋል።
- መመሪያውን ማሻሻል በተመለከተ ክፍል ላይ መመሪያው በማንኛውም ወቅት እንደሚሻሻል ተደንግጓል። ይህ ግን የባለፍቃዶችን ጥቅም ስለሚጎዳ ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ቢፈጠር።
- ጉልህ ድርሻ የሚለው ቃል ትርጓሜ ክፍል ላይ ቢካተት እና ትርጉም ቢሰጠው፤
- በመመሪያው ላይ የተመለከቱ እና ትርጓሜ የሚያሰፈልጋቸው ቃላቶች ትርጓሜ ቢሰጣቸው።
- በመመሪያው ላይ መሰረተ ልማት ወይም ኮሎኬሽን የሚጋሩት ኦፕሬተር ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ቀርቧል። ይህ ግን ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎችን የሚያገል በመሆኑ መሻሻል ቢደረግበት፤
- በዘርፉ ኢትዮቴሌኮም ገበያው ላይ ጉልህ ድርሻ ያለው ተብሎ ይገለጽ፤

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የቴክኖሎጂውን መስፋፋት የሚኖረውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በመክትት የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል፡-

- ኢትዮቴሌኮም በዘርፉ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ መመሪያው ላይ ይመልከት ተብሎ የተነሳው ጥያቄ ተገቢ አይደለም። አንድ ኦፕሬተር በአንድ ዘርፍ ላይ ጉልህ ደርሻ አለው የሚባለው በአዋጁ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ኦፕሬተር ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ በመመሪያ አይወሰንም። ምክንያቱም ዛሬ ላይ ጉልህ የኘበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተሰየመው ኦፕሬተር ነገ ላይ ላይሆን ስለሚችል።
- የኮሎኬሽን እና የመሰረተልማት መጋራት ጥያቄዎች ደህንነትን ከግንዛቤ የከተተ መሆን አለበት የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ያለው ሲሆን ይህ ግን ሃገሪቱ ባወጣቻቸው ሌሎች ህጎች በቂ ምላሽ ያገኝ በመሆኑ እዚህ ቦታ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።
- መግቢያው ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል።

- ጉልህ የገበያ ድርሻ የሚለው ቃል በዚህ መመሪያ ፍቺ ይሰጠው የሚለው ጥያቄ በአዋጁ ላይ ምላሽ ያገኘ በመሆኑ እዚህ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል። በዚህም መሰርት ባለሰልጣኑ መመሪያውን ከማሻሻሉ በፊት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል።
- በመመሪያው ውስጥ ለተካተቱ እና ፍቺ ለሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ፍቺ ተሰጥቷቸዋል።

## 6. ለውይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የመጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ

- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያውን በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በመጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያውን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሐሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር። ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በመሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።
- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው መሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት። ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል። ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሐሳቤ/ አስተያት ተገቢ በመሆኑ በዛ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል።

- በመመሪያው ላይ መሰረተ ልማት ወይም ኮሎኬሽን የሚጋሩት ኦፕሬተር ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ቀርቧል። ይህ ግን ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎችን የሚያገል በመሆኑ መሻሻል ቢደረግበት የሚል ሐሳብ ከተሳታፊዎች ቀርቧል። ሃሳቡ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ እና የመመሪያው ዋና ግብም ኦፕሬተር ላይ ብቻ ያተኮረ ባለመሆኑ፤ ማሻሻያ ተደርጓል።

- በመድረክ ተሳታፊዎች ፍቺ የሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን ለእነዚህ ቃላቶች ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል አንቀ 2(1፣2፣3፣9፣10፣14 )።